# የቤተ መፃሕፍት ማህበራትና ተቋማት ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽን

## የኢንተርኔት ማኒፌስቶ

መረጃን ባልተገደበ ሁኔታ ማግኘት ለነፃነት፣ ለእኩልነት፣ ለዓለም አቀፋዊ መግባባትና ለሰላም እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው:: በመሆኑም የቤተ-መፃሕፍት ማህበራትና ተቋማት ዓለም-አቀፍ ፌዴሬሽን የሚከተለውን ይገልፃል::

- ምሁራዊ ነፃነት አመለካከትን የመያዝና የመግለጽ እንዲሁም መረጃን የመፈለግና የመቀበል የእያንዳንዱ ግለሰብ መብት ከመሆኑም በላይ የዲሞክራሲ መሰረት ነው:: በተጨማሪም በቤተ-መፃሕፍት አገልግሎት ውስጥ አንዱ ዐቢይ ተግባር ነው::

- መረጃን የማግኘት ነፃነት መረጃው የሚገኝበት መንገድ ወይም ድንበር ሳይወስነው የቤተ መፃሕፍትና የኢንፎርሜሽን ሙያ ዋነኛ ኃላፊነት ነው::

- በቤተ-መፃሕፍትና በመረጃ አገልግሎቶች አማካይነት ባልተገደበ ሁኔታ ቀርቦ የሚገኝ የኢንተርኔት አጠቃቀም ማህበረሰቦችና ግለሰቦች ነፃነትን፣ ብልጽግናና ዕድገትን እንዲያገኙ ይረዳል::

- የመረጃ ፍሰትን የሚገድቡ ሁኔታዎች ሊወገዱ ይገባል፤ በተለይም እነዚህ ገደቦች እኩል ያለመሆንን፣ ድህነትንና ተስፋ መቁረጥን የሚያራምዱ በሆነ ጊዜ::

## መረጃን የማግኘት መብት፣ ኢንተርኔት እና የቤተ መፃሕፍትና የመረጃ አገልግሎቶች

ቤተ-መፃሕፍትና የመረጃ አገልግሎቶች ህዝቦችን ከመላው ዓለም የመረጃ አገልግሎቶች የሚያገናኙ ጠቃሚ ሃይል ያላቸው ተቋማት ከመሆናቸውም በላይ እጅግ የካበተውን የሰውን ልጅ እሳቤና ባህላዊ የልዩነት ውበት በሁሉም ዓይነት ሚዲያ የሚያቀርቡ ናቸው::

ዓለም-አቀፍ ኢንተርኔት በመላው ዓለም ውስጥ የሚገኙና በትናንሽ ወይም እጅግ ርቀው በሚገኙ መንደሮች ውስጥ ከሚገኙ እስከ ትላልቅ ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ማህበረሰቦችና ግለሰቦች ለግላዊ ዕድገት፣ ለትምህርት፣ ለመዝናናት፣ ለባህላዊ ብልጽግና፣ ለኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴና በዲሞክራሲ ውስጥ በመረጃ ለተደገፈ ተሳትፎ መረጃን በእኩልነት እንዲጠቀሙ የሚያስችል ነው።

ቤተ-መፃሕፍትና የመረጃ አገልግሎቶች ወደ ኢንተርኔት የሚያቀርቡ እጅግ ጠቃሚ ሥፍራዎች ናቸው። አንዳንዶች እነዚህን ሥፍራዎች ከአመቺነት፣ ድጋፍና እርዳታን ከማግኘት አንፃር የሚመርጧቸው ሲሆን ለሌሎች ደግሞ ብቸኛ የመጠቀሚያ ሥፍራዎች ናቸው። በመሆኑም ቤተ-መፃሕፍትና የመረጃ አገልግሎቶች በሃብት፣ በቴክኖሎጂና በሥልጠና ልዩነት ምክንያት የተፈጠረውን ክፍተት የሚሞሉ ናቸው።

## በኢንተርኔት አማካይነት የሚተላለፉ መረጃዎችን የማግኘት ነፃነት መርሆዎች

በኢንተርኔትና በውስጡ በሚገኙ አጠቃላይ የዕውቀት ሃብቶች የመጠቀም ጉዳይ ከተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችና በተለይም ከአንቀጽ 19 ጋር የተጣጣመ መሆን ይገባዋል። ይህ አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል፡-

*ሁሉም ሰው የራሱን አመለካከት የመያዝና ይህንኑም የመግለጽ ነፃነት አለው። ይህ ነፃነት ማናቸውንም አመለካከት ካለአንዳች ጣልቃ ገብነት የመያዝ፣ እንዲሁም ማናቸውንም ዓይነት ሚዲያ በመጠቀምና በድንበር ሳይወሰን መረጃዎችንና አሳቤዎችን መፈለግ፣ መቀበልና ማስተላለፍን የሚያጠቃልል ነው።*

በአሁኑ ጊዜ የሚገኘው ዓለም- አቀፉ የኢንተርኔት ጥብቅ-ጥምረት ሁሉም ወገኖች በዚህ ነፃነት እንዲጠቀሙበት አመቺ የመጠቀሚያ መንገድ ፈጥሮአል። በመሆኑም በኢንተርኔት የመጠቀም ሁኔታ ማናቸውም ዓይነት የአይዲዮሎጂ፣ የፖለቲካ ወይም ሃይማኖታዊ ቁጥጥር /ሳንሱር/ ወይም ኢኮኖሚያዊ ገደብ ሊደረግበት አይገባም።

ቤተ-መፃሕፍትና የመረጃ አገልግሎቶች የእድሜ፣ የብሔር፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣ የፖለቲካዊ ወገናዊነት፣ የአካላዊ ወይም ሌላ ጉዳት፣ የጾታ ወይም ሌሎች ማህበረሰባዊ ደረጃዎች ሳይወስኗቸው ሁሉንም የማህበረሰባቸውን አባላት የማገልገል ተጨማሪ ኃላፊነት አለባቸው::

ቤተ-መፃሕፍትና የመረጃ አገልግሎቶች የተጠቃሚዎችን መረጃዎችን እንደምርጫቸው የመፈለግ መብት መደገፍ ይኖርባቸዋል::

ቤተ-መፃሕፍትና የመረጃ አገልግሎቶች የተጠቃሚዎቻቸውን ግላዊነት ማክበር የሚጠበቅባቸው ሲሆን ተጠቃሚዎቹ የሚገለገሉባቸው የኢንተርኔት መጠቀሚያዎች ግላዊ ምሥጢራዊነት የተጠበቀ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል::

ቤተ-መፃሕፍትና የመረጃ አገልግሎቶች ህብረተሰቡ ጥራቱ የተጠበቀ የመረጃና የመገናኛ አገልግሎት እንዲያገኝ ሁኔታዎችን የማመቻቸትና ለዚሁም ተግተው የመሥራት ኃላፊነት አለባቸው:: ተጠቃሚዎች የሚፈልጉትን የመረጃ ምንጭና አገልግሎት ነፃ በሆነና በሙሉ መንፈሥ መጠቀም ይችሉ ዘንድ አመቺ በሆነ የመጠቀሚያ አካባቢና የተሟላ ዕውቀት ባላቸው ሠራተኞች ሊረዱ ይገባል::

በኢንተርኔት ውስጥ የሚገኙ አገልግሎቶች ብዙዎቹ ጠቃሚ መሆናቸው የሚታወቅ ቢሆንም  አንዳንዶቹ ግን ስህተት ያለባቸው፣ አሳሳችና አስነዋሪ ናቸው:: ተጠቃሚዎች በኢንተርኔትና በኤሌክትሮኒክ መረጃዎች በብቃትና በውጤታማነት እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ለማስተማር ይቻል ዘንድ የቤተ-መፃሕፍት ባለሙያዎች መረጃዎችንና መርጃ መሣሪያዎችን ሊያቀርቡላቸው ይገባል:: እንዲሁም ህፃናትንና ወጣቶችን ጨምሮ ሁሉም ተጠቃሚዎች ሃላፊነት በሚሰማው ሁኔታ ጥራቱ የተጠበቀ የኔትወርክ መረጃ ማግኘት እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ለዚሁም በንቃትና በትጋት መሥራት ይጠበቅባቸዋል::

ለሌሎች ዐቢይ አገልግሎቶች እንደሚፈፀመው ሁሉ በቤተ-መፃሕፍትና በመረጃ አገልግሎቶች ውስጥ ኢንተርኔትን መጠቀም ከክፍያ ነፃ መሆን ይኖርበታል::

## ማኒፌስቶውን ሥራ ላይ ስለማዋል

በኢንተርኔት አማካይነት መረጃ ለሁሉም በመላው ዓለም እየተዳረሰ የሚገኝበትን ጠቀሜታ ማግኘት ይችሉ ዘንድ የኢንተርኔት አቅርቦት በሁሉም አገሮች በተለይም በማደግ ላይ በሚገኙት አገሮች መስፋፋቱን እንዲደግፉ የቤተ-መፃሕፍት ማህበራትና ተቋማት ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽን ዓለም-አቀፍ ማህበረሰቡን ያበረታታል።

ብሔራዊ መንግሥታት ለሁሉም የሃገራቸው ዜጐች የኢንተርኔት አገልግሎት ማዳረስ የሚችል ብሔራዊ የመረጃ መሠረተ-ልማት መገንባት እንዲችሉ ፌዴሬሽኑ ያበረታታል።

የቤተ መፃሕፍት ማህበረሰብ አባላትና እንዲሁም በብሔራዊና በአካባቢ ደረጃ የሚገኙ ውሳኔ ሰጭ አካላት በዚህ ማኒፌስቶ ውስጥ የተጠቀሱትን መርሆዎች በተግባር ለመተርጐም የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን፣ ፖሊሲዎችንና ዕቅዶችን እንዲያዘጋጁ ፌዴሬሽኑ ጥሪ ያቀርባል።

---

ይህ ማኒፌስቶ በቤተ-መፃሕፍት ማህበራትና ተቋማት ዓለም-አቀፍ ፌዴሬሽን እና በፌዴሬሽኑ ሥር በተደራጀው "መረጃን በነፃ የማግኘትና ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ ኮሚቴ" የተዘጋጀ ነው። ማኒፌስቶው እ.ኤ.አ ማርች 27 ቀን 2000 በሄግ ኔዘርላንድስ በፌዴሬሽኑ ገዥ ቦርድ ፀድቆ እ.ኤ.አ ሜይ 1 ቀን 2000 በይፋ ተገለፀ።

ማኒፌስቶው እ.ኤ.አ ኦገስት 23 ቀን 2002 በግላስጐ ስኮትላንድ በተካሄደው የፌዴሬሽኑ 68ኛ ጠቅላላ ጉባኤና ካውንስል ካለአንዳች ተቃውሞና ድምፀ-ተአቅቦ በሙሉ ድምጽ ፀድቋል።